# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የገጠር አካባቢዎችን ተደራሽ የሚያደርገው ድሬደዋ ቁጥር-3 የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ

በለጥሻቸው ልዑልሰገድ

የድሬደዋ ቁጥር-3 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በምስራቅ ሪጅን ቁጥር አንድ ካሉት የሀይል ማከፋፈያ ጣቢያዎች መካከል አንዱ ነው። ይህ ጣቢያ በተደረገለት የማስፋፊያ ግንባታ በርካታ የገጠር አካባቢዎችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል። እኛም በዚህ ሳምንት እትማችን ይህንን ሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ አስመልክቶ ከጣቢያው ሃላፊ አቶ አበባው አበራ እና በምስራቅ ሪጅን የሰብስቴሽን ሜንቴናንስ ፕሮቴክሽን ሠራተኛ የሆኑት አቶ ግርማ ደቻሳ ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አዘጋጅተን አቅርበናል።

በድሬደዋ ቁጥር አንድ የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የነበሩ ፓወር ትራንስፎርመሮች ከ26 ሜጋ ዋት በላይ መጫን ባለመቻላቸው በ1981 ዓ.ም የድሬደዋ ቁጥር ሶስት የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ግንባታ መጀመሩን የሚናገሩት በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ምስራቅ ሪጅን ቁጥር አንድ የሰብስቴሽን ሜንቴናንስ ፕሮቴክሽን ሠራተኛ የሆኑት አቶ ግርማ ደቻሳ፤ የጣቢያው ግንባታ በ1987 ተጠናቆ ወደ ስራ መግባቱንና ጣቢያው ስራ የጀመረው ከቆቃ የሃይል ማመንጫ 230 ኪሎ ቮልት በቀጥታ በማስገባት መሆኑን ይገልፃሉ።

ጣቢያው በዓለም ባንክ ድጋፍ በሚደረግለት በኢትዮጵያን የገጠር አካባቢዎች ኤሌክትሪክ ተደራሽ የማድረግ ፕሮጀክት አማካይነት በተሰራ ማስፋፊያ አንድ ባለ 16 MVA ትራንስፎርመር ተተክሎ በ33 ኪሎ ቮልት ለፋብሪካዎችና ዙሪያውን ላሉ የገጠር አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ሃይል ተደራሽ ማድረግ ተጀመረ። ይህ የማከፋፈያ ግንባታ የተከናወነው የገጠሩ ክፍል ከከተማ በብዙ ርቀት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ረጅም ርቀት ላይ ያሉ አካባቢዎችን ተደራሽ ለማድረግ ታስቦ እንጂ በወቅቱ ጣቢያው የሃይል እጥረት ኖሮበት እንዳልነበርም ጨምረው ያስረዳሉ።



አቶ ግርማ ደቻሳ



አቶ አበባው አበራ

በድሬደዋ ቁጥር-3 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ሃላፊ የሆኑ አቶ አበባው አበራ፤ የድሬደዋ ቁጥር-3 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ለምስራቅ ኢትዮጵያ፣ ለምስራቅ ሃረርጌ እንዲሁም በከፊል ለሱማሌ ክልል፤ ጅቡቲን ጨምሮ ኤሌክትሪክ ተደራሽ ለማድረግ ለሚሰራው ስራ ትልቅ ሚና የሚጫወት ጣቢያ ነው። ይሄ ጣቢያ የለም ማለት በአብዛኛው የምስራቅ ኢትዮጵያ ክፍል መብራት የለም ማለት ነው። ይህ የኤሌክትሪክ ማከፋፈያ ጣቢያ ጅግጂጋ፣ ከሃረር እስከ ደገሃቡር፣ ምስራቅ ሃረርጌ፣ ሂርና፣ ሀሮማያ እና ጅቡቲን ጨምሮ አብዛኛውን የገጠሩን ክፍል የሚሸፍን የኤሌክትሪክ ኃይል አገልግሎት የሚሰጥ ነው ይላሉ።

እንደ ሃላፊው ገለፃ፤ የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያው ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በስራ ላይ የሚገኝ ሲሆን ለድሬደዋ ከተማ የአሌክትሪክ ሀይል በማከፋፈል ረገድ የሚጠበቅበትን ሚና ሲጫወት ቆይቷል፤ አሁንም ኻይል በማከፋፈል ላይ ይገኛል። ይህ የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ከአዋሽ ሰባት የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ 230 ኪሎ ቮልት ተቀብሎ ባሉት የባለ 132 እስከ 15 ሺህ ኪሎ ቮልት ወጪ መስመሮች አማካኝነት ለድሬደዋ ቁጥር 1 እና 2 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ኃይል የሚሰጥ ነው።

ድሬደዋ ቁጥር-1 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ የተቀበለውን 132 ኪሎ ቮልት ወደ ትራንስፎርመር በማስገባት 15 ሺህ ኪሎ ቮልት ያወጣል። ይህንን 15 ሺህ ኪሎ ቮልት ለድሬደዋ ከተማ ነዋሪዎች በሙሉ በማሰራጨት ተደራሽ ያደርጋል። በተጨማሪም ለናሽናል ሲሚንቶ 132 ኪሎ ቮልት ይሰጣል።

ድሬደዋ ቁጥር 2 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያም እንዲሁ የተቀበለውን 132 ኪሎ ቮልት ወደ ሀረር የማከፋፈያ ጣቢያ ይልካል። ሀረር የማከፋፈያ ጣቢያ በትራንስፎርመሮቹ አማካኝነት ለሀረር ከተማ እና ለአካባቢው ማህበረሰብ እንዲሁም ለሀረር ቢራ ፋብሪካ እና ለሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ሃይል ያሰራጫል። ከዚህ በተጨማሪ 132 ኪሎ ቮልት ወደ ጅግጅጋ ከተማ ይልካል። ጅግጅጋ ላይ ያለ ማከፋፈያም የተቀበለውን 132 ኪሎ ቮልት ለጅግጅጋ ከተማ እና በዙሪያዋ ለሚገኙ ከተሞ ያከፋፍላል።

ድሬደዋ ቁጥር-3 የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ተጨማሪ 33 ኪሎ ቮልት በጣቢያው አቅራቢያ ለሚገኙት ቱሬ የሲሚንቶ ፋብሪካ፣ ሸሙ ሳሙና ፋብሪካ እና ፓይነር ሲሚንቶ ፋብሪካ እንደሚሰጥ የሚናገሩት ሃላፊው፤ ጣቢያው 15ሺህ ኪሎ ቮልት ተጨማሪ ወጪ መስመር ያለው ሲሆን ለመልካ ጀብዱ፣ ለኩባ ካንፕ እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ሃይል የሚሰጥ ጣቢያ መሆኑን ይናገራሉ።

ይህ ጣቢያ 2002 ዓ.ም ሰፊ የማስፋፊያ ግንባታ የተካሄደበት ሲሆን፤ ጅቡቲ፣ አዲጋላ ሃይል ማከፋፈያ እና አይሻ የንፋስ ሃይል ማመንጫ የሚደርስ የመስመር ዝርጋታ ተካሂዷል። የማስፋፊያ ስራውም ሶስት ዓመት የፈጀ ነበር። በ2003 ዓ.ም ወደ ጅቡቲ ሃይል ኤክስፖርት ማድረግ የተጀመረው ከዚህ የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ሲሆን ከ30 እስከ 40 ሜጋ ዋት የሚደርስ ሃይል ወደ ጅቡቲ ይልክ ነበር። የጅቡቲ የሀይል ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ ሁርሶ የሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ እንዲገነባ ተደረገ። የሁርሶ ሃይል ማከፋፈያ ጣቢያ በመገንባቱ የድሬደዋ ቁጥር 3 ሃይል ማከፋፈያ ጣቢያን ጫና በእጅጉ መቀነስ ችሏል ሲሉ አክለው ይገልፃሉ።